# ለድህረ ምረቃ ትምህርት ፈላጊዎች በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የቀረበ ልዩ ገጸ-በረከት

አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ አንጋፋው የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሲሆን በተለያዩ የ3ኛና የ2ኛ ዲግሪ መርሃ-ግብሮች ተማሪዎችን ተቀብሎ ማሰልጠን ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በ2017 የትምህርት ዘመን ከመቼውም ጊዜ በላይ በታላቅ አክብሮትና ደስታ አመልካቾችን ለመቀበል ተዘጋጅቷል፡፡

## አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ያቀረባቸው ልዩ እድሎች፡-

ሀገር አቀፍ የድህረ-ምረቃ ትምህርት መግቢያ ፈተናን (NGAT) ላለፉ የ3ኛና የ2ኛ ዲግሪ አመልካቾችን የሚከተሉ ልዩ ማበረታቻዎችና ድጋፎች ይጠብቃሉ፡-

- ✓ የሁለተኛም ሆነ የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች አማካሪዎቻቸው በሚይዙት የ1.75 ሚሊዮን ብር ግራንድ ፕሮጀክቶች የመካተት እድል፤
- ✓ ሁሉም የሶስተኛ ዲግሪ አመልካቾች በ Small scale ፕሮጀክት ለ175,000 ብር ወንዶች እና ለ185,000 ብር ሴቶች የምርምር ድጋፍ ለማግኘት የማመልከት እድል፤
- ✓ በግል ለሚማሩ የሁለተኛ ዲግሪ አመልካቾች 25, 000 ብር የምርመር መስሪያ ገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት የመወዳደር እድል፤

- ✓ ተማሪዎቻችን ዩኒቨርሲቲው ያመቻቸውን አለም-አቀፋዊ የመረጃ ቋት (https://www.fundsbeeline.com) ተጠቅሞ ለሶስተኛ ዲግሪ ምርምራቸው ከተለያዩ አለም-አቀፍ ዩኒቨርስቲዎችና የምርመር ማዕከላት የገንዘብ ድጋፍ እና ከሙሁራን ጋር የልምድ ልውውጥ ማግኘት ዕድል፤
- ✓ ለአካል ጉዳተኛ አመልካቾች ልዩ የምርምር መስሪያ ገንዘብ ድጋፍ፤
- ✓ ደረጃቸውን ጠብቀው የተደራጁ ቤተ-መጻህፍትን እንዲሁም ዩኒቨርሲቲው የመጠቀም ፈቃድ ያገኘባቸውን ውድ አለም-አቀፍ ኤሌክትሮኒክ የምርምር ውጤቶችን በነጻ የመጠቀም እድል፤
- ✓ ለምርምር ስራ የተሟሉ ላቦራቶሪዎችን በሁሉም ግቢዎች የመጠቀም እድል፤
- ✓ ነጻ የመረጃ መረብ ተደራሽነት (wifi internate) በሁሉም ግቢዎች፤
- ✓ ለሁሉም አመልካቾች በአነስተኛ ክፍያ የመኝታ አገልግሎት (dormitory) እና
- ✓ ለሁሉም አመልካቾች በተመጣጣኝ ክፍያ ከካፍቴሪያዎች የምግብ አገልግሎት የማግኘት እድል፤

**ማሳሰቢያ፡- በማንኛውም የNGAT መፈተኛ ማዕል ፈተናውን ወስዶ ያለፈ አመልካች በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ለመማር ማመልከት ይችላል፡፡**